# <u>የኢህአፓ መግለጫ!</u>

ከጌታቸው ቀጀላ

የሀገር ጥፋት፤ የሀገር ውድመት፤ የህዝብ ጉስቁልና፤ ያየር መዛባት፤ ሁሉም በዚህ ትውልድ ጫንቃ ላይ ተፈናጠው እየተፈታተኑት የሚገኙ ክስተተቶች ናቸው። በዚህ ጊዜ የመኖር ዕድል አግኝቶ በዓይን እየተመለከቱ ፊትን ማዞር ምናልባትም ከሀገራዊ ስሜትም ሆነ ከተፈጥሮአዊ ህልውና ጎራ ሊያስመድብ የሚችል አይሆንም። ምክንያቱም ይህን መሳዩን አደጋ መቋቋም የሰብአዊነትም የዜግነትም ግዴታ ጭምር በመሆኑ። ኢህአፓ በዚህ መግለጫው ላይ ያስተላለፈውን ታላቅ መልዕክት በአንክሮ ሊመለከቱት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል። ጥሪው የግል ድርጅቴን ደግፉልኝ፤ ገንዘብ አዋጡልኝ አይደለም። ጥሪው የሚገልፀው የሀገርን የተዋሳሰበ ችግር ለመወጣት ቁራጥና የተባበረ ትግል ማስፈለጉን ነው። ለዘህ አይነቱ ትግል ለተነሳ የተቃዋሚ ድርጅት ኢህአፓ ከጎኑ እንዳለ በመጠቆም፤ በወያኔ የማዋዣ ምርጫ መሳተፍ በህዝብ መብት ላይ እንደማሾፍ የሚቆጠር መሆኑን አመላክቶ፤ ህዝባችንን በዚህ አይነቱ የወያኔ ትያትር እንዳይዋዛ እናስጠነቅቃለን የሚል መሆኑን ተረድቻለሁ። በእርግጥ ትህትናን በተላበሰ መልኩ ልዩነቱን አስቀምጦ ለዓላማው እንደሚሰራ መግለፅ ከእያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት የሚጠበቅ ነው። ህዝብን ለማሳሳት ደባ መፈፀም ግን ይቅር የማይሉት ወንጀል ነው። የኢህአፓ መግለጫ  ህዝብን የጠራ ግንዛቤ እንዲኖረው ስለሚያደርግ እጅጉን የሚያስመሰግን ነው።

ኢህአፓ በእርግጥም ከህዝብ ስሜትና መብት ያፈነገጠ ትግል አድርጎ አያውቅም። ህዝብ መብቱን የማስከበር ዐቅሙ ሲዳከም፤ ኢህአፓም ተዳክሟል። ህዝብ መብቱን የማወቅ አቅሙ እንዲጎለብትና ለመብቱ መቆም አስፈላጊነቱን እንዲገነዘበው ለማድረግ ግን አንድም ጊዜ ወደሁዋላ ብሎ አያውቅም። ከህዝብ ወገኖች ጋር ይወግናል፤ የህዝብንም ጠላቶች ከህዝብ ጋር ሆኖ ይፋለማል። ይህ የኢህአፓ የማያወላዳ የህዝብ ፍቅሩ መገለጫ ለመሆኑ ታሪኩ ይመሰክራል። በባዕዳን ዳረጎት ተገዝቶ፤ ለአምባገነኖች ጭፍጨፋ እጅ ሰጥቶ ህዝብ ሲሰቃይና በርሀብ ሲያልቅ፤ ህዝብ መብት አልባ ሆኖ ሲገዛ እየተመለከተ እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። በከተማም በገጠርም አቅሙ በፈቀደ መጠን ከውጭ ተገዥነትና መልዕክተኛነት በፀዳ መልኩ የህዝብን ጠላት ሲፋለም ቆይቷል። ያን ሁሉ የመከራ ዘመን በፅናቱ አሳልፎ እነሆ! ህዝቡ ካንዱ ስቃይ ወደ ሌላ ስቃይ እየተላለፈ ሲመጣ፤ ኢህአፓም ለጠላቶቹ አጎብድዶ፤ በጠላቶቹ እጅ ወድቆ ሊከዳው አልተዘጋጀም። ከህዝቡ ጋር ሆኖ ካንድ መከራ ወዳንዱ እየተላለፈ በፅናቱ የቆየ ድርጅት በመሆኑ ዛሬም በህዝብ ላይ ማሾፍ ቢቀር ይሻላል እያለ ምክሩን እየለገሰ ነው። አሁንም ከህዝቡ ጋር መቆሙን እያስመሰከረ። አሁንም ለህዝቡ መብት እየተሟገተ ነው። ብራቮ ኢህአፓ! የህዝብ አለኝታነትህን ደጋግመህ አስመስከር ልንለው ይገባል!!

ኢትዮጵያ በነፃነቷ ኮርታ ለዘለዘም ትኑር!